

በየነ ገበረ ተስፋ

ከታሪክ ማህደር 1።

# ማን ያርዳ የቀበረ፣ ማን ይናገር የነበረ፣

ይህ የዛሬ ወደ ሁለት ዓመት አከባቢ ኢህአፓ/ሰ ከብተና እስከ ፍጻሜው በሚል ርእስ ስር በተከታታይ ስተርክው ከነበረ ክፍል 20ን እንደገና ለማቅረብ ያስገደደኝ አቶ ዓምዶም ገብረስላሴ የድሮ የኢህ አፓ አባል ነበር የተባለው አቶ ሙሉወርቅ ኪዳነማሪያም ስለ ትግራይ መገንጠል የተናገረውን መሰረት አድርጎ የጻፈውና በተደጋጋሚ የተለጠፈው ጽሁፍ ነው።

ኢህ አፓእንደ ማንኛውም ከ1966ቱ አቢዮት በኋላ ለውጥ ለማምጣት ብለው የታገሉ ድርጅቶች ያራሱ የሆኑ ድክመቶች፣ ስህተቶችና ችግሮች የነበሩት ድርጅት ቢሆንም፣ በብሄር ጥያቄ ላይ እስከ መገንጠል የሚል የብሄሮች መብት በመብት ደረጃ ቢቀበልም በኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ ላይ ግልጽ አቋም ይዞ የታገለ፣ በዚህ አቋሙም በጠባብ ብሄረተኞች በተለይ (በህወሓትና ሻዕቢያ) ከጅምሮ ጀምሮ በተለይ ደግሞ ከደርግ መወገድ በኋላ በጋራ በተስነዘረበት የማጥፋት ዘመቻ በርካታ አባላቱ ተሰውተው የቀሩት እንዲሰደዱ የተደረገ መከረኛ ድርጅት ነው። ለሁሉም ራሳችሁ አንባቢዎች እንድትፈርዱት ዛሬም ኢህ አፓ ነኝ የሚል ሆነ፣ የኢህ አፓ አባል ነበርኩ የሚል ኡነተኛ የኢህአፓ ልጅ በብሄር ጥያቄ ላይ ያለው/የነበረው አቋም ምን ይመስል ነበር የሚለውን ማወቅ ለምትፈልጉ ቀጥሎ የተቀመጠውን እንድታነቡ እጋብዛችኋለሁ።

ክፍል ሃያ ስድስት ፣

መሰረታዊ የአቋሞች ለውጥ የተደረገበት የኢህአፓ/ሰ ሁለተኛ ጉባኤ በቋራ በረሃ፣

ኢህ አፓ/ሰ በ1974 ቋራ ገብቶ በቋራ አላጢሽ በሚባለ በረሃ ቤዙን ከመሰረተና ካጠናከረ በኋላ፣ በሱዳን በኩል ከውጭ ጋራ የነበረው ግኑኝነቱን መስርቶ በውቅቱ በአውሮጳና አመሪካ ከነበሩ አባላቱ ግኑኝነት ካደረገ በኋላ ግንባር ቀደም ተልእኮው አድርጎ የወሰደው ያለፈበት የ12 ዓመት የትግል ጉዞዉን በሚገባ ገምግሞ ለቀጣዩ ትግል ለመዘጋጀት ለብዙ ዓመታት በተለያዩ ምክንያቶች ሳይከሄድ ቆይቶ የነበረውን ጠቅላላ ጉባኤን ማዘጋጀትና ማካሄድ ላይ ነበር።

ለ1976ቱ ጠቅላላ ጉባኤ ዝግጅቱ የተጀመረው ገና በ1975 መባቻ ሆኖ ዝግጅቱ በሁሉም መስኩ ከተጠናቀቀ በኋላ ከኤውሮጳም ከአመሪካም ጥቂት አባላት የተገኙበት በአብዛኛው ከሱዳንና ሜዳ የነበሩ የፓርቲው አባላት በስፋት የተሳተፉበት የኢህአፓ ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባኤ በ1976 መጋቢት ላይ በቋራ በረሃ አካሄደ።

በዚህ ከወር በላይ በወሰደው ጉባኤ ድርጅቱ ከምስረታው 1964 እስከ 1976 ለ12 ዓመታት የተጓዘው የትግል ጉዞ ውስጥ የተከሰቱ ድክመቶች፣ ስህተቶች፣ ችግሮችና ጥንካሬዎች በጥልቀት ተገመገሙ፣ ዓለም አቀፋዊ፣ አከባቢያዊና ሃገራዊ ሁኔታዎችም በጥልቀት ተመረመሩ፣ በወቅቱ ከነበሩ ዓለም አቀፋዊ፣ አከባቢያዊና ሃገራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች አንጻር ድርጅቱ በቆየው የፖለቲካ ፕሮግራሙ ነጥብ በነጥብ ተወያይቶ መስተካከል የነበርባቸው ተስተካከሉ፣ መጨመር የነበረባቸው አዲስ አቋሞች ተጨመሩ፣ መለወጥ የነበረባቸውም ተለወጡ፣ ለረጂም ጊዜ በተለያየ ችግር ምክንያት ስይሟላ የቆየው የድርጅቱ አመራር (ማእከላዊ ኮሚቴ) በባለት የድምጽ አሰጣጥ ስንስርዓትም በአባላት ተመረጠ።

የኢህአፓ አባላት ከላይ እስከታች በዚህ ሁለተኛ ጉባኤው ስለ ድክመቶች፣ ስህተቶችና ጥንካሬዎቹ ሲገመግም፣ ከዛ በፊት በሚደረጉ በነበሩ ስብሰባዎች ሲታዩበት ከነበሩት ቀኖናዊነት፣ ምስጥራዊነትና ስሜታዊነት ርቀው ነበር ግምገማውን በስፋትና በጥልቀት ያካሄዱት። ከግለሰብ እስከ ቡድን በድርጅቱ ውስጥ የተከሰቱ ድክመቶች፣ ስተቶችና ግችሮች ያለ

ምንም ፍርሃትና ይሉኝታ ነበር የተገመገሙት። የኢትዮጵያ አቢዮት ከመስፍናዊ አገዛዝ መገርሰስ በኋላ በነበሩት 12 ዓመታት የተጓዘው ጉዞና የሚገኝበት የነበረ ደረጃ፣ የብሄር ጥያቄ፣ የዴሞክራሲ ጥያቄ፣ የህብረት ትግል ጥያቄ፣ የቅራኔዎች አፈረጃጀትና የወቅቱ ዓብይ ቅራኔ፣ በኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ላይ በወቅቱ ጸረ ደርግ ትጥቅ ትግል ሲያካሄዱ በነበሩ ጠባብ ብሄርተኛ ድርጅቶች አማካይነት እያንጃበበ የነበረው አደጋ፣ በጠባብ ብሄርተኛ ድርጅቶች አማካይነት በህዝቦች መካከል እየተዘራ የነበረው የጥላቻ መርዝና መዘዙ፣ . . . ወዘተ. በመሳሰሉ ጥያቄዎች ላይ በተለያዩ አቅራቢዎች ጥናታዊ ትንታኔዎች ቀርበባቸው ከግልብና ቀኖናዊ አመለካከት በጸዳ መንገድ ጥልቅ ውይይትና ክርክር ተደርጎባቸው በዴሞክራሲያዊ መንገድ በርካታ ውሳኔዎችና የአቋም ለውጦችም የተደረጉበት ጉባኤ ነበር።

የቋራው የኢህ አፓ ሁለተኛ ጉባኤ ከወር በላይ ጊዜ የወሰደ ጉባኤ ሆኖ ከድርጅቱ የፖለቲካ ፕሮግራም ነጥቦች፣ የብሄር ጥያቄ፣ የመሬት ጥያቄ፣ የኢኮኖሚ ጥያቄ፣ የዴሞክራሲ ጥያቄ፣ የህብረት ትግል ጥያቄ ላይ የአቋም ለውጥ በዚህ ጉባኤ ወሳኔዎች መሰረት ተደርጓል። ከደርግ መወገድ በኋላ በኢትዮጵያ ኡነተኛ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ከተፈለገ፣ በተለያየ ጎራ ተሰልፈው በተፋለሙና እርስ በርስ በተጋደሉ ድርጅቶች መካከል ከወዲሁ ዕርቀ ሰላም ለማውረድ መሰራት እንዳለበት፣ ገና ደርግ ከመወገዱ በፊት እንዴት ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንሸጋገር በሚለው ስምምነት ላይ መደረስ እንዳለበት፣ ሁሉንም የሚመለከታቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች አሳታፊ የሆነ የሽግግር መንግስት መመስረት ግዴታ እንደሆነ በኢህ አፓ ታምኖበት ለዚህ መስራት መጀመር እንዳለበት የተወሰነው በዚህ በቋራው ሁለተኛ ጉባኤ ነበር።

በጉባኤው ውሳኔዎች መሰረት የአቋም ለውጥ/ማሻሻል የተደረገባቸውና አዲስ የተጨመሩ ነጥቦች የሚከተሉት ነበሩ።

ሀ. የብሄር ጥያቄን በተመለከተ፣

ከጉባኤው በፊት የብሄርና ብሄረሰብ መብት እስከ መገንጠል ድረስ ይቀበላል የሚል የነበረው የኢህ አፓ አቋም ከጉባኤው በኋላ ጠባብ ብሄረተኛ ድርጅቶች እስከ መገንጠል የሚለውን ዓለም አቀፍ የብሄሮችና ብሄረሰቦች መብት ድንጋጌን በመጠቀም ከኢትዮጵያ ህዝቦች ፍላጎት ውጭ ለቡድናዊ/ድርጅታዊ ፍላጎታቸውና ጥቅማቸው እየተጠቀሙበት እንደሆነ ድርጅቱ በጊዜው አውቆ ኢህ አፓ ትምክህተኝነትን ለማጋለጥ እንደዘመተው ሁሉ በጠባብ ብሄርተኝነት አደጋ ላይም ገና ከጅምሩ አለመዝመቱ እንደ ስህተት ተቀብሎ በብሄር ጥያቄ ስም የተደራጁ ጠባብ ብሄርተኛ ድርጅቶች በኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ላይ ሊያሳድሩ የምችሉትን አደጋ በውል በመገንዘብ መገንጠልን እንደ መብት በፕሮግራሙ ማስቀመጥ ትክክል አይደለም ተብሎ መገንጠል የሚለው ቃል ከፕሮግራሙ እንዲወጣና በአንዲት የጋራ ሃገር በእኩልነት መኖር በሚለው እንዲተካ ተወሰነ። ከጉባኤው በኋላም በትምክህተኝነት ላይ እንደተዘምተው ሁሉ በብሄር ጥያቄ ስም ለግል ቡድናዊ ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው ለማሟላት ደርግን በትጥቅ ትግል ሲዋጉት በነበሩ ጠባብ ብሄርተኛ ድርጅቶች ላይም ቀጣይነት ያለው የፖለቲካ ትግል መካሄድ እንዳለበትና በተለይ በወቅቱ ድርጅቶቹ እንታገልልህ አለን ከሚሉት ከነበረው ህዝብ ማንነታቸውን በማጋለጥ መነጠል እንደሚያስፈልግ ተወሰነ። በወቅቱም ደርግን በትጥቅ ትግል ሲዋጉት የነበሩት ህወሓት፣ ሻዕቢያና ኦነግ በጠባብ ብሄርተኛ ድርጅቶች ደረጃ ተፈረጁ።

ለ. የመሬት ጥያቄን በተመለከተ፣

መሬት በኢህ አፓ የሚመሰረተው ሶሽያሊስት መንግስት ቁጥጥር ስር ሆኖ ለህዝቡ በእኩል መከፋፈል አለበት የሚል የነበረው አቋም ተሰርዞ፣ መንግስት ከመሬት ባለቤትነት ጥያቄ እጁን ማንሳት አለበት፣ መሬት የኢትዮጵያ ህዝብ አንጡራ ሃብት መሆን አለበት፣ የገጠሩ መሬት የገበሬው የግል ንብረቱ ሆኖ ገበሬ በመሬቱ እስከ መሸጥ ድረስ ያለው የተሟላ መብት ባለቤት መሆን በግልጽ መቀመጥ አለበት፣ የከተማ መሬትም እንዲሁ የነዋሪው ህዝብ ንብረትነቱ ተረጋግጦ፣ ባለመሬቶቹ መሬታቸው የመሸጥ፣ መለወጥና ማውረስ ሙሉ መብት መረጋገጥ አለበት፣ በህዝብ ያልተያዙ ድንግል መሬቶች፣ ፓርኮች፣ ታላላቅ ወንዞች፣ ሃይቆች . . . የመሳሰሉ መሬቶች በህዝብ በሚመረጥ መንግስት ቁጥጥር ስር ሆነው ለህዝቡ አግልግሎት መዋል አለባቸው በሚል እንዲተካ ተአረገ።

ሐ. የኢኮኖሚ ጥያቄ በተመለከተ፣

ከሁለተኛ ጉባኤ በፊት የነበረው ኢኮኖሚው በሶሺያሊስት ፓርቲ በሚመራው መንግስት ቁጥጥር ስር መሆን አለበት የሚል አቋም የነበረው ሲሆን፣ ይህ አቋም በጉባኤው ተሻሽሎ ሀገሪቷ መከተል ያለባት የኢኮኖሚ ፖሊሲ የቅይጥ ኢኮኖሚ፣ (Mixed Economy) (መንግስትንና የግል ባለሃብትን የሚያሳትፍ ኢኮኖሚ) መሆን አለበት በሚለው ተሻሻለ። ይህ የቅይጥ ኢኮኖሚ ፖሊሲ አዲስና በተለይ የሶሺያሊስት አይዲዮሎጂ ተከታይ ነን በሚሉ የነበሩ የሃገራችን የግራ አይድዮሎጂ ተከታይ ድርጅቶች ብዙ የማይታወቅና ተቃውሞም የነበረበት አቋም ስለነበረ፣ ኢህ አፓ እንደ አንድ የሶሺያልዝም አይድዮሎጂ ተከታይ የግራ ድርጅት ለምን የቅይጥ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ለኢትዮጵያ አስፈላጊ ነው ይላል የሚለውን ለህዝቡ በቀጣይነት ለማስተማር፣ ቅይጥ ኢኮኖሚ፣ ቅይጥ ሂደት፣ ቅይጥ ጎራ በሚል ርእስ በተከታታይ በመጽሄትና በበራሪ ወርቀቶች እንዲሁም ህዝባዊ ስብሰባዎች አማካይነት ለህብረተሰቡ ሰፊ ትምህርት እንዲሰጥበትም ተወሰነ። ኢህ አፓ በጉባኤው ውሳኔ መሰረት ስለ ቅይጥ ኢኮኖሚ ህብረተሰቡን ማስተማር እንደጀመረ፣ አይዲዮሎጅያችን ሲሽያሊዝም ነው ሲሉ የነበሩ ጠባብ ብሄረተኛ ድርጅቶች በተለይ ህወሓት ኢህ አፓ የሶሽያሊዝምን አይድዮሎጂዉን ሸጦ፣ ጭቁኖችን (ላባደርና አርሶ አደሩን) ክዶ ወደ የቡርጁዋ ፓርትነት ተቀይሯል በማለት የቂይጥ ኢኮኖሚ ፖሊስውን ማጥላላትና ማንቋሸሽ ጀመሩ።

በተለይ በህወሓት ውስጥ በ 1977 የተፈጠረው ማሌሊት ኢህ አፓ የሶሽያሊስቶችን ካምፕ ክዶ ወደ የቡርጁዋ ካምፕ ገብቷል በማለት፣ ኢህ አፓ ወጣ ወጣና እንደ ሸንበቆ፣ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ በሚል ርእስ በተከታታይ ጸረ ኢህ አፓ ቅስቀሳ በተከታታይ በጽሁፍም በስብሰባዎችም በሱዳንና በትግራይ በስፋት ይቀሰቅስ ጀመረ። ኢህ አፓም በበኩሉ የህወሓት/ማሌሊት መንቦጫረቅ ሳይሉ ፈቅ በሚል ርእስ በህወሓት ውስጥ የተፈጠረው በስመ ሶሺያሊስት አይድዮሎጂ የምነግደው ጸረ ኢትዮጵያ ቡድን አደገኛነትና መሰሪነት በስፋትና በቀጣይነት በመጺሄቶች፣ ዴሞክራሲያና በራሪ ወርቀቶች እንዲሁም ህዝባዊ ስብሰባዎች አማካይነት ማጋለጡን ቀጠለ። በተለይ በሁለቱ ኢህ አፓና ህወሓት/ማሌሊት ብዙ ኢትዮጵያዊ ስደተኛ ይኖርበት በነበረው ሱዳን ዘመቻው በሁለቱም በኩል ከጉባኤው ማግስት (1967- 1983) እስከ ደርግ መገርስስ ተጠንክሮ ቀጥሎ የኢህ አፓ አቋም በሱዳን በነበረው ስደተኛ ራሱ የህወሓት/ማሌሊት ደጋፊዎች ጭምር ከፍተኛ ድጋፍና ተቀባይነት ማግኘት ጀመሮ ነበር።

መ. የዴሞክራሲ ጥያቄ በተመለከተ፣

ከጉባኤው በፊት የነበረ አቋም በሲሽያሊት ፓርቲ የሚመራ (የአንድ ፓርት/ሶሺያሊስት ፓርቲ) ተለክቶ የሚሰጥ ዴሞክራሲ የሚፈቅድ የነበረ ሲሆን፣ ከጉባኤው በኋላ በአንዲት ሃገር በትክክል ዴሞክራሲ መስፈን አለበት ከተባለ በሀገሪቷ የተለያየ አይዲዮሎጂ የሚከተሉ የተለያዩ ፓርቲዎች ህልውናና ነጻ ፉክክር የግድ ነው። ስለሆነም ኢህ አፓ የሶሺያልዝም አይዲዮሎጂ ተከታይነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በኢትዮጵያ ሌላ ዓይነት አይዲዮሎጂ የሚከተሉ ደርጆቶች ህልወናም ተቀብሎና አክብሮ ለዚህ ተግባራዊነት ይታገላል በሚለው ተቀየረ፣ ለዚህ ተግባራዊነትም ከጉባኤው ማግስት ጀምሮ መንቀስቅቀስና መስራት ተጀመረ።

ሠ. የህብረት ትግልን በተመለከተ፣

ከጉባኤው በፊት ከሶሺያልስት አይድዮሎጂ በመነሳት የህብረት ትግል ሲነሳ የህብረት ትግል መመስረት የሚገባው የሶሺያልስት/ግራ አይዲዮሎጂ ከሚከተሉ ድርጅቶች ጋራ ነው መሆን ያለበት የሚል የነበረው አቋም፣ በቋራው ሁለተኛ ጉባኤ ተቀይሮ፣ በወቅቱ በነበረው የቅራኔዎች አፈረጃጀት መሰረት ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን በጠምንጃ ሃይል ረግጦ እየገዛ ያለውን ፋሽስታዊ የደርግ አገዛዝንና የሶቬት ህብረት ጣልቃገብነትን በዋና ጠላትነት ተፈርጀው፣ የፋሽስቱን አገዛዝ ለማስወገድ ከሚታገሉ ሃይሎች ሁሉ የህበረት ትግል ለማካሄድ ኢህ አፓ ዝግጁ ሆኖ ለዚህ ተግባራዊነት መስራት አለበት በሚል ተሻሻለ። በወቅቱ በኢህ አፓ የቅራኔዎች አፈረጃጀት፣ ፋሽስቱ የደርግ አገዛዝና የሶቪየት ጣልቃ ገቢነት በአንድ

በኩል፣ የኢትዮጵያ ሰፊው ህዝብ በሌላ በኩል የተሰለፉበት ነው የሚል ነበር።፣

ረ. የሽግግር መንግስት ጥያቄን በተመለከተ፣

እስከ ጉባኤው የነበረው የፓርቲው አቋም፣ ደርግን አስወግዶ በሶሽያሊስት ፓርቲ/ኢህ አፓ በሚመራ መንግስት መተካት አለበት የሚል ነበር። ከቋራው ሁለተኛ ጉባኤ በኋላ ግን ኢህ አፓ፣ የአንድ ፓርቲ ስርዓት አብቅቶ የብዙሃን ፓርቲ ስርዓት በኢትዮጵያ መመስረት አለበት የሚል አቋም ያዘ። ከደርግ ፋሽስታዊ አገዛዝ መወገድ በኋላ አገዛዙን በተለያየ ድርጅት ተደራጅተው ሲፋለሙ የነበሩ ድርጅቶች በመካከላቸውም ብዙ ደም መፋሰስ ስለተፈጸመ ይህ ሁሉ ችግር የሚፈቱበት፣ በመካከላቸው እርቀሰላም የሚፈጥሩበት፣ የፖለቲካ ፕሮግራማቸው በሰላማዊ መንገድ ከዝቡ ጋራ የሚያስተዋውቁበት፣ ከሁሉም የሚመለከታቸው ድርጅቶች፣ የሃገር ሽማግሌዎች፣ምሁራን በጋራ የሚሳተፉበት የሽግግር ጊዜና መንግስት መኖር የግ ነው የሚል አዲስ አቋም በጉባኤው ጸደቀ። ከጉባኤው ማግስት ጀምሮም ኢህ አፓ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች/ከፍሎች ጋራ በሽግግር ፕሮግራሙ መሰረት ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር መኖር የሚደረገው ጉዞ ገና ከጅምሩ በሁሉም ባለጉዳዮች በጋራ እንዲጀመር እንቅስቃሴ ጀመረ።

ኢህአፓ በቋራው ሁለተኛ ጉባኤው ከላይ የተቀመጡት የአቋም መሻሻሎችና ለውጦችን በፕሮግራሙ አድርጎ ፋሽታዊ ደርግን አስወግዶ በኢትዮጵያ ወደ ዴሞክራሲ የሚደረገው የሽግግር ጉዞ ገና በጸረ ደርግ ትግሉ ወቅት በሁሉም ጸረ ደርግ ሃይሎች መካከል እንዲደረግ እንቅስቃሴውን የጀመረው ከጉባኤው ማግስት ጀምሮ ነበር። በወቅቱ ኢህ አፓ በርግጥ በብሄር ጥያቄ ስም ተደራጅተው ደርግን ሲታገሉ የነበሩ ጠባብ ብሄረተኛ ድርጅቶች (እንደ ሻዕቢያ፣ ህወሓት፣ ኦነግ) በሁለተኛ ደረጃ ጠላትነት ፈርጆ የነበረ ቢሆንም ከነሱ ጋራ የሚደረገው ትግል ከፖለቲካ ትግል ያለፈ በትጥቅ ትግል ፈጽሞ መሆን የለበትም የሚል አቋም ነበረው።

ስለሆነም እነሱንም ሲደረግ በነበረ ጸረ ደርግ የህብረት ትግል እንዲጨመሩ፣ እንዲሁም ከደርግ መወገድ በኋላ በሚመሰረተው የሽግግር መንግስት ጅግጅትም ገና ከጅምሩ እነሱም እንዲጨመሩ የተለያየ ጥሪትና ጥሪ አድርጎላቸው ነበር። ሆንም ግን በወቅቱ ደርግ እየተዳከመ እነሱ ደግሞ በጸረ ኢትዮጵያ የባዕድ ሃይሎች እየታገዙ በትጥቅ ትግሉ በኩል በፍጥነት እያደጉ የሚሄዱበት ሁኔታ ተፈጥሮላቸው ስለነበረ የኢህ አፓና ከኢህ አፓ ጋራ ግንባር ፈጠረው ሲታገሉ የነበሩ በወቅቱ በኢዴሃቅ ስር ተሰባስበው የነበሩ ሃይሎች ጥሪ ሳይቀበሉ ቀሩ።

በመጨረሻም ደርግ በኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል ተገዝግዞ ገደል አፋፋ ላይ ደርሶ ስለነበረ በጸረ ኢትዮጵያ የባዕድ ሃይሎች ተደግፈው ገደል አፋፍ ላይ ደርሶ የነበረውን ደርግ ገፍትረው አስውግደው ኢትዮጵያያዊ አቋም የነበራቸውን ሃይሎች በሙሉ ውጭ አስቀርተው፣ ኤርትራን ከኢትዮጵያ አስገንጠለው፣ ህወሓት የሚፈልጋቸውን ጠባብ ብሄረተኛ ድርጅቶችን ብቻ አሳትፈው የሽግግር መንግስት ትብዬ መስርተው፣ ከዛም ህወሓት የሚቆጣጠረው አገዛዝ በኢትዮጵያ መስርተው የኸው ዛሬ ሃገራችንና ህዝቦቿ ደርሰውበት ላለው አጣብቂ ሁኔታ ኢትዮጵያን አደረሷት።

## ከታሪክ ማህደር 2

ዛሬ ሃገራችንና ህዝቦቿ ገብተውበት ካለው እጅግ አሳሳቢ አጣብቅኝ ሁኔታ ለመውጣት የሚደረገው ትግል የትናንቱን ስህተት እንዳይደግም፣ በደርግ ለመውደቅ እያኮበኮበ በነበረበት በ 1980 ዎቹ መጀመሪያ የነበረው ሁኔታ ምን ይመስል እንደነበረ ባጭሩ ላሳያችሁና እንድትወያዩበት፣ ያኔ የተደረገው ዓይነት ስህተት እንዳትፈጽሙና ከኢህ አዴግ መወገድ በኋላ መደረግ ያለበትን ካሁኑኑ በሁሉም እንዲታሰብበትና እንዲሰራበት ለማሳሰብ ወደድኩ።

ክፍል ሃያ ስምንት፣

ከ 1980-1983 ኢህ የአፓ/ሰና ተባባሪዎቹ መሰረታዊ ዓላማና የትግል አቅጣጫ ምን ነበር።

የኢህ አፓ/ሰና ተባባሪዎቹ ዓላማና የትግል አቅጣጫየትግል አቅጣጫ ምን ይመስል ነበር የሚለውን ከመተረኬ በፊት፣ ኢትዮጵያን ለ17 ዓመት የገዛው ወታደራዊ ደርግ ውድቀት እየተቃረበ መሆኑ ግልጽ እየሆነ መጥቶ የነበረ ቢሆንም የውድቀቱን የቁልቁለት ጉዞ ከተገመተው በላይ እጅግ ያፋጠነውና ለደርግ አገዛዝ በዛ ፍጥነት ለመገርሰስና ኢትዮጵያና ህዝቦቿ በኢህአዴግ ስም ላልፉት 26 ዓመታት እየገዛ ባለው ህወሓት ስር በቀላሉ ለመውደቅ ዋና ምክንያት የሆነው የኢትዮጵያ ሰራዊት ከፈተኛ መሪዎች በ1981 የሞከሩት መፈንቅለ መንግስት መክሸፍና ኮሎነል መንግስቱ ኃይለማሪያም የመፈንቅለ መንግስቱ መሪዎች ናቸው ባሉዋቸው የሰራዊቱ መሪዎች ላይ የፈጸሙት ግዲያ እንዴት ሰራዊቱን ያለ አመራር አስቀርቶ እንዳሽመደመደውና ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው በወቅቱ ደህና የታጠቀ ሰራዊት ገንብተው የነበሩ ህግሓኤ/ሻቢያና ህወሓት በጸረ ኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት የዓረብ መንግስታትና በአመሪካ በሚመራወ በምዕራቡ ዓለምም ከፈተኛ ሁለገብ እርዳታ በመታገዝ ሁኔታውን እንደተጠቀሙበት ባጭሩ ትንሽ ልበል።

በ1970ዎቹ መጨረሻ ደርግ በኢትዮጵያ ህዝቦች ለ14 ዓመታት በወሰደው ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ፣ አፈናና እስራት ምክንያት በሀገሪቷ በሙሉ በኢትጵያዊያን ሁሉ አከ እንትፍ ተፍሎ የተተፋበት ሁኔታ ተፈጥሮ ስለነበረ የደርግ ውድቀት እየተቃረበ መሆኑ እንኳን ሁኔታዎችን በቅርበት በራሳቸው ኢንተልጀንስ አማካይነት እየተከታተሉ ደርግን ለማስወገድና የመንግስት ስልጣን ለመያዝ ሲታገሉ የነበሩ ድርጅቶች ቀርቶ ሁኔታውን በቅርበት ለሚከታተል ተራ ዜጋም ግልጽ እየሆነ መጥቶ ነበር። በተለይ ጸረ ደርግ ትጥቅ ትግል ሲያካሄዱ የነበሩት ህግሓኤና ህወሓት ሲንቀሳቀሱበት በነበረው ኤርትራና ትግራይ ክለሃገራት ደርግ አማጽያኑንና ህዝቡን ሳይለይ ሲወስዳቸው በነበረው ፋሽስታዊ ድብደባዎች፣ ወጣቱን የአማጺያኑ ደጋፊ ነህ በማለት በየጊዜው ማንገላታ፣ መግደልና ማሰር ምክንያት ህዝቡ ሳይወድ በግድ ከአማጺያኑ ጎን በመቆም ደርግን የሚዋጋበት ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ አድጎ ደርግ በሁለቱ ክፍለ ሃገራት በተወሰኑ ትልልቅ ከተሞች ብቻ የተወሰነበትና ሞላው ገጠሩና በርካታ ትንንሽ ከተሞች በአማጺያኑ ቁጥጥር ስር የወደቁበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር።

ሁኔታው በእንዲህ እያለ በ1981 ግንቦት 8 ላይ የኢትዮጵያ ሰራዊት ከፈተኛ መኮነኖች በኮሎነል መንግስቱ ኃይለማሪያም ሲመራ የነበረውን የደርግ ቡድን ለመገልበጥ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ አደረጉ። ለዝርዝሩ "ጀነራሎቹ" በሚል ርእስ በሻምበል ኢዮብ አባተ እንዳለ የተጻፈውን መጽሃፍ ማንበብ እጅግ ጠቃሚ ነው። በዚህ መፈንቅለ መግስት ሙከራ ምክንያት የመፈንቅለ መንግስቱ ጠንሳሾችና ደጋፊዎች ናችሁ በመባል በርካታ ከፈተኛ የጦሩ መሪዎች የነበሩ ከፍተኛ መኮነኖችና ደጋፊዎቻቸው ናቸው የተባሉ ዝቅተኛ መኮነኖች በኮሎነል መንግስቱ ትእዛዝ መሰረት በ1981 ላይ በብዛት እንዲገደሉ ተደረገ፣ የተቀሩት በርካቶች ደግሞ በቁጥጥር ስር ዋሉ።

በዚህ ግዲያና እስራት ምክንያትም በኤርትራና ትግራይ ህግሓኤንና ህወሓትን ሲዋጋ የነበረው የኢትዮጵያ ሰራዊቱ የዳበረ ዕውቅትና ተመክሮ የነበራቸውና በጦሩም ይወደዱና ይከበሩ የነበሩ ወታደራዊ መሪዎቹን እንዲያጣና ካለ መሪዎች እንዲቀር ተደረገ።

በ1982 ሰኔ ላይ በአዲስ አበባ በእስር የነበሩት የመፈንቅለ መንግስቱ ዋና ጠንሳሾች ናቸው የተባሉ ከፍተኛ የጦሩ መሪዎች በኮለነል መንግስቱ ትእዛዝ መሰረት እንዲረሸኑ ተደረገ። የነዚህ ከፈተኛ የሰራዊቱ መሪዎች መረሸን ደግሞ ሰራዊቱ በኮሎኔል መንግስቱ በሚመራው የደርግ አገዛዝ ላይ የነበረው እምነት እጅግ እንዲላላና የመዋጋት ፍላጎቱም እጅግ እንዲቀንስ አስደረገ። ከ1982 ግንቦት እስከ 1983 ግንቦት የደርግ ሙሉ በሙል መገርሰስ በነበረው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ ሰራዊት ከህግሓኤና ህወሓት ጋራ ባካሄዳቸው ጦርነቶች ሁሉ እንደበፊቱ ጠንክሮ መዋጋቱን አቁሞ ገና ውግያው እንደተከፈተ ብዙዎቹ እጅ መስጠ ወይም መሸሽ ብቻ ሆነ። ይህን ሁኔታ በሚገባ ያወቁትና በወቅቱ በክፍለጦር ደርጃ የተደራጀ ጦር እየመሰረቱ የነበሩ፣ በራሱ በደርግ መንግስት ውስጥ ከላይ እስከ ታች የራሳቸው የእንተልጀንስ መዋቅር ፈጥረው ሲንቀሳቀሱ የነበሩና በጸረ የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት የነበሩ የዓረብ መንግስታትና በአመሪካ በሚመራው ምዕራባዊ ዓለም በተለይ በእንግሊዝና ጣሊያን በሁሉም መስኩ በከፈተኛ የማተሪያልና የኢንተልጀንስ ድጋፍ ሲያገኙ የነበሩ ህግሓኤና ህወሓት በኤርትራና በትግራይ በሰራዊቱ ላይ የማያቋርጥ ተከታታይ ጦርነት ከፈቱ።

የኤርትራና የትግራይ ገጠራማ አከባቢን ለመቆጣጠረ ወደ 16 ዓመት ወስዶቦቸው የነበረው፣ ኮሎነል መግስቱ

ኃይለማሪያም የሰራዊቱ ከፈተኛ ወታደራዊ መሪዎች በመፈንቅለመንግስት ሰበብ ካስገደሉ በኋላ፣ ሰራዊቱ ካለ አመራር ከቀረ በኋላም በአንድ ዓመት ጊዚ ውስጥ ሞላው ኤርትራና ትግራይን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረው፣ ከትግራይ በመንደርደር ወደ ማኸል ኢትዮጵያ ለመግባት ዝግጅት ጀመሩ።

በወቅቱ በህወሓትና በህግሓኤ ስም ከትግራይና ኤርትራ ውጭ ተቀባይነት እንደማያገኙ ስላወቁም ከኢህ አፓ/ሰ ተለይተው ኢህዴን መስርተው ሲታገሉ የነበሩትን፣ በኤርትራና በትግራይ ተማርከው በህግሓኤና ህወሓት ስር ከነበሩ የጦር ሙርከኞች በ 1983 የካቲት ላይ ኢህ አዴግ የሚባል ግንባር መስርተው እነዛ የኢህዴንና የሙርኾኞቹ አባላትን በመጠቀም የደርግ አገዛዝን አክ እንትፍ ብሎ ተፍቶት የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ በርኩን ክፍቶላቸው ህወሓት በኢህ አዴግ ስም አዲስ አበባን ህግሓኤ ደግሞ አስመራን በ 1983 ግንቦት ላይ ተቆጣጠሩ።

በወቅቱ በኢህአፓና ተባባሪዎቹ በኩል የነበረው እንቅስቃሴስ ምን ይመስል ነበር፣

ከ 1980- 1983 ባለው ጊዜ ኢህ አፓ ከመጀመሪያ የጉሪላ የትጥቅ ትግል የዕድገት ደረጃ ወደ ሁለተኛ የጉሪላ የትግል ደረጃ ተሸጋግሮ ሰራዊቱን በባታሊዮኖች ደርጃ አደራጅቶ፣ ወደ 6 ተዋጊ ባታሊዮች፣ በጥሩ ደረጃ የተደራጀ ራስን በራስ መቻል (Self Reliance) ክፍል፣ በውጭ በሱዳንና አመረካ በደህና ደረጃ የተደራጀ የፓርቲ መዋቅርና እንቅስቃሴ፣ በሃገርቤትም በ 1960 ዎቹ መጨረሻ በኋላ በከተሞች ተቋርጦ የነበረውን መዋቅሩን እንደገና በማዋቀር ለረጂም ጊዜ ተቋርጦ ከነበረው ከተወሰኑ አባላቱ በተለያዩ ከተሞች ግኑኝነት መመስረት የተጀመረበትና በአዳንድ ከተሞችም መዋቅሮቹን እንደገና በመመስረት ላይ የነበረበት፣ ከቋራ ሲተላለፍ በነበረው ፍኖተ ዴሞክራሲ ረዲዮ አማካይነት ደግሞ መልእክቱን ለሞላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለማስተላለፍ የቻለበትና እንደ ድርጅትም አባል የነበረበት ትብብር/ኢዴሃቅ በውጭ በተለይ በአመሪካና ኤውሮጳ የነበረውን ስደተኛ በስፋት ከጎኑ በማሰለፍ በፍጥነት እያደገና እየተጠናከረ የነበረበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነበር።

ኢህ አፓ በ 1976 ቱ ጉባኤው የአቋም ለውጥ ሲያደርገ የማይቀረው የፋሽስቱ ደርግ ውድቀት እየተቃረበ መሆኑ አውቆ ከዛ ጉባኤ ማግስት ጀምሮ ከተናጠል ትግል ይልቅ የጋራ ትግል ላይ አተኩሮ፣ ደርግን ለማስወገድ ብቻ ሳሆን ደርግ ከተወገደ በኋላ የሃገር አንድነትና ሉዓላዊነት ተጠብቆ፣ ወደ ዴሞክራሲያዊ ህዝባዊ ስርዓት የሚደርገ ሽግግር ገና ከወዲሁ በትግሉ ሜዳ በጋራ ለመጀመር ከሁሉም ጸረ ደርግ አማጺያን ጋራ በጋራ ለመስራት ወስኖ ነበር የሚንቀሳቀሰው።

በቋራው የኢህ አፓ ሁለተኛ ጉባኤ የአቋም ለውጥ ሲደረግ እስከዛው በኤርትራ ጥያቄ ላይ በብሄር ጥያቄ ዙሪያ መታየት አለበት ከሚል የዘለለ በግልጽ የተብራራ ከነመፍትሄው አመላካች አቋም ያልያዘበት የኤርትራ ጥያቄ- ደፍሮ የብሄር ጥያቄ ነው፣ የኤርትራ ችግር መፈታት ያለበት ደግሞ በፈደራላዊትና ዴሞክራሲያዊት ረፑብሊክ ኢትዮጵያ ስር ነው በሚል ግልጽ አቋም ወስዶ የኤርትራ ሁኔታ ከድሮ ጀምሮ ሂደቱን በመዘርዘር አስቀምጦ በልሳኑ በዴሞክራሲያ በአማርኛም በትግርኛ ተተርጉሞ ይህን አቋሙ ኤርትራዊያንም ጨምሮ ለኢትዮጵያዊያን በረዲዮውም በስብሰባዎችም ግልጽ እያደረገ መታገል ሁሉ ጀምሮ ነበር። በዚህ አቋሙም ህግሓኤና ህወሓት እጅግ ተበሳጭተው ኢህአፓ ላይ የበለጠ ጥርስ ሲነክሱ፣ በበርካታ ኢትዮጵያዊያንና ኤርትራ የተለየች ሃገር ናት ሲሉ በነበሩ ኤርትራዊያንም አቋሙ ከፈተኛ ተቀባይነት እያገኘ በምሄድ ላይ ነበር።

ኢህአፓ በኤርትራ ጥያቄ ላይ ያኔ የወሰደው አቋም ምን ይመስል እንደነበረ ለማወቅ የምትፈልጉ ዝርዝሩን ቀጥሎ በተቀመጠው ሊንክ መሰረት ወደ ያ ትውልድ ድረገጽ ገብታችሁ ማየት ይቻላል።

http://yatewlid.com/i…/Demo_Vol_15_Liyuetm_Meskerem_1982.pdf

ኢህ አፓ የህብረት ትግል ከሌሎች ድርጅቶች ጋራ ፈጠረን መታገል አለብን ብሎ በቋራው የ 1976 ጉባኤው ሲወስን ለኢህ አፓ አባላት ሌላ ከፈተኛ ፈተና የነበረው እነዶክተር ነገደ ጎበዜ ከሚመሩት መኢሶን፣ ኮሎነል ጎሹ ወልዴ ሲመሩት ከነበሩት የኢትዮጵያ መድህን ፓርቲ፣ በትግራይና በወልቃይት ኢህ አፓ/ሰን የወጋውን የህወሓት ጦር ሲመሩ ከነበሩ እነ ግደይ ዘርዓጺዮንና ኣረጋዊ በርሀ የሚመሩት ከነበረው የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር ዓይነቶቹ ብዙ ደም ከተፋሰሱና ከፈተኛ ቂምና ጥላቻ በመካከላቸው ተፈጥሮ ከነበረው ድርጅቶች ጋራ ያ ቂምና ጥላቻ ተሻግሮ በጋራ በትብብር እንታገል

ወደሚለው ውሳኔ መድረስ ነበር። ከላይ ከተጠቀሱት ድርጅቶች ጋራ የተባበረ ትግል ማካሄድ አለብን ወደሚለው የጋራ ውሳኔ ለመድረስ ከባድና እልህ አስጨራሽ ክርክር ነበር የተካሄደው።

በመጨረሻ ግን እንዝ በከተሞችም በሜዳም የወደቁ የኢህ አፓ/ሰ ሰማዕታት ዛሬ በህይወት ቢኖሩና ሃገር በአንድ ከግል ስልጣኑ ውጭ ፈጽሞ ማየት በማችል አንድ ፋሽስት ግለሰብ ቁጥጥር ስር ወድቃ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለብዙ ዘመናት ተከብሮ የኖረውን አንድነቷና ሉዓላዊነቷን ለመበታተን የቋመጡ ጠባቦች በብሄር ጥያቄ ስም ተነስተው በፍጥነት እያደጉና ሃገሪቷን ለመበታተን በሩጫ ላይ ያሉበት ይህን ሁኔታ ቢያዩ ኑሮ ይህ አሁን እኛ ከምንወስነው የተለየ ውሳኔ አይወስኑም ነበር።

ከዚህ በተጨማሪም እነዛ ሰማዕታት ውድ ህይወታቸውን የከፈሉት በኢትዮጵያ የተሟላ ዴሞክራሲ ለማስፈን እንጂ የአንድ ፓርቲ አምባገነንነትን ለማስፈን ፈጽሞ አልነበረም፣ አሁን እኛ በዕድል በህይወት የተረፍን የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ተከብሮ የተሟላ ዴሞክራሲ ስርዓት በኢትዮጵያ ለማስፈን ከሌሎች ትናንትና ደም ከተቃባናቸው ባንድነት ለመታገል መወሰን ሰማዕታቶቻችን የተሰዉለት ዓላማ እግቡ ማድረስ ስለሆነ ከድርጅት በፊት ሃገርንና ህዝብን አስቀድመን ከጥላቻና ቂም በቀል ወጥተን ትናንትና ጠላቶቻችን ብለን ከፈረጅናቸው፣ ዛሬ ግን ልክ እንደኛው ሀገሪቷንና ህዝቦቿን ከፋሽስቶችም ከጠባቦችም ለመታደግ አብረዉን መታገል ከሚፈልጉት ጋራ ተባብረን ከመታገል ውጭ ዛሬ ሌላ አማራጭ የለም የሚለው ሃሳብ ሁሉንም አስማምቶ በዚህ ስምምነት መሰረት ነበር ኢህ አፓ ከሁለተኛ ጉባኤው በኋላ በሙሉ ሃይሉ ለትብብር ትግሉ (ለኢዴሃቅ ዓላማ ማሳካት) ሲንቀሳቀስና ሲሰራ የነበረው።

በኢህአፓ ከፈተኛ አስተዋጽኦ ኢዴሃቅን ብ 1982 መጀመሪያ በጋራ በካናዳ የመሰረቱ ድርጅቶች፣ (ኢህ አፓ፣ መኢሶን፣ ኢዴህ፣ ኢፒዲኤ፣ ኢመፓና ትዴት) ገና ከምስረታው በፊት በሚመሰረተው ትብብር ውስጥ ሁሉም ተቃዋሚ ሃይሎች በምስረታው ገና ከጅምሩ ለማሳተፍ ሲንቀሳቀስ የነበረ የኢህ አፓ ማኮ ልኡክ ማንንም ሳያገል ለሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች ጥሪውን አቅርቦ ነበር። ጥሪ ከቀረበላቸው መካከልም ህግሓኤ/ሻዕቢያ፣ ህወሓትና ኦነግ ነበሩ።

በል ኡኩ በምስረታው ስብሰባ እንዲገኙ ጥሪ ከቀረበላቸው ድርጅቶች ህግሓኤና ኦነግ ገና ከጅምሩ እኛ ከኢትዮጵያ ባዕዳዊ አገዛዘ ነጻ ለመውጣት የምንታገል ድርጅቶች ስለሆን ከኢትዮጵያዊያን ድርጅቶች ጋራ ደርግን ለማስወገድ ከሚደረገው ትብብር የዘለለ ሌላ የሚያገናኘን ነገር የለምና ጥሪው እኛን አይመለከተንም ብለው በግልጽ በመናገር ጥሪውን ሳይቀበሉት ቀሩ። ህወሓት ግን በመጀመሪያ ጥሪውን እንደሚቀበልና በምስረታው ስብሰባም እንደሚገኝ አስታውቆ በካናዳ በተካሄደው የምስረታው ስብሰባ ላይ ሳይገኝ ቀረ። በዚህ ምክንያትም በምስረታው ስብሰባ በተገኙት በኢህአፓ፣ መኢሶን፣ ኢፒዲኤ፣ ኢዴህ፣ ኢመፓና ትዴት ኢዴሃቅ ተመሰረተ።

ከኢዴሃቅ ምስረታ በኋላ በውጭም በሃገርቤትም የሚደረጉ የነበረ ጸረ ደርግ ትግል በትብብሩ ስም ሆነው የትብብሩ ዓላማ ለኢትዮጵያዊያን በውጭም በሃገርቤትም ለማስተዋወቅና ኢትዮጵያዊያን ትብብሩን እንዲደግፉና እንዲቀላቀሉ በኢህ አፓ አባላት ሰፊ እንቅስቃሴ ተደርገ። በዚህ እንቅስቃሴም ኢዴሃቅ በውጭ በተለይ በአማሪካ፣ ኤውሮጳ እንዲሁም በሱዳን ባጭር ጊዜ ውስጥ ሰፊ ድጋፍ እያገኘ መጣ። በሃገር ቤትም በፍኖተ ረዲዮና በተለየዩ በራሪ ጽሁፎች ኢዴሃቅን ለማስተዋወቅ ጥሩ እንቅስቃሴ ተካሂዶ ሻዕቢያ በስፋት ሲቆጣጠረው ከነበረው ኤርትራና እንዲሁም ህወሓት ሲቆጣጠረው ከነበረው ትግራይ ውጭ በነበረው የኢትዮጵያ ክፍል በተለይ በከተሞች ኢዴሃቅ እየታወቅና ጥሩ ተቀባይነት እያገኘ መሄድ ጀምሮ ነበር።

ሁኔታው በእንዲህ እያለ በ 1981 በተካሃደው መፈንቅለ መንግስት ምክንያት ኮሎነል መንግስቱ ኃይለማሪያም የኢዮጵያ ሰራዊት መሪዎች ወዲያውኑ በብዛት ካስገደሉና የተቀሩትንም በ 1982 በፍርድ ስም ካስረሸኑ በኋላ ሁኔታዎች እጅግ ተገለባበጡ። የኢትዮጵያ ሰራዊት ህወሓትና ህግሓኤ ጦርነት ሲከፍቱበት መልሶ መዋጋት አቆሙ መሸሽና እጅ መስጠት ብቻ ሆነ፣ ደርግ ቆሞበት የነበረው ዋናው ሙሶሶ ጦር ሰራዊቱ በአመራር እጦትና በኮሎነል መንግስቱ በሚመራ በነበረው የደርግ ቡድን ላይ ተስፋ በመቁረጡ ፈጽሞ ባልተጠበቀው እጅግ ከፍተኛ በፍጥነት ባጭር ጊዜ ውስጥ መናድ ጀመረ።

ሰራዊቱ ከተናደ በኋላ፣ የኢትዮጵያ ህዝብና የተለያዩ ድርጅቶች ኢህ አፓን ጨምሮ ለ 17 ዓመታት ባካሄዱት መራራ ተጋድሎ ተቦርብሮ ለመውደቅ አፋፍ ላይ ደርሶ በመንገዳገድ የነበረው የደርግ አገዛዝን በወቅቱ በነበራቸው ጠናካራ ሰራዊትና በባዕዳን ሁለገብ እርዳታ ህግሓኤና ህወሓት ለመውደቅ ገደ አፋፍ ላይ ደርሶ የነበረውን የደርግ አገዛዝን ገፍትረው ወደ ገድል በመከተት ህግሓኤ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ የመንግስት ስልጣን ያዘ፣ ህወሓትም በኢህ አዴግ ስም በተቀረው ኢትዮጵያ የመንግስቱን ስልጣን ያዘ።

ለህግሓኤና ህወሓት በወቅቱ እንዲህ በቀላሉ ደርግን አስወግደው የመንግስት ስልጣን ለመያዝ የረዳቸው ሌላው ምክንያት ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ደርግ የሚባል ጉግ ማንጉግ ይወገድ እንጂ ከዛ በኋላ የፈለገው ይምጣ የሚል ደረጃ ላይ ደርሶ መኖርና የህግሓኤና የህወሓት መሪዎች መሰሪነትና ገና ከውልደታቸው ጀምሮ የነበራቸው ጸረ የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት አቋም ጠንቅቆ አለማወቅ ነበሩ። በወቅቱ ሁለቱ ድርጅቶች ከኤርትራና ትግራይ ውጭ በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ህዝባዊ ድጋፍ ቀርቶ በወሬ ወሬ ካልሆነ በህዝቡ ብዙ እውቅናም አልነበራቸውም።
ይህ ሆኖ እያለ ህዝቡ በደርግ በነበረው የመረረ ጥላቻ ምክንያት ስለ ማንነታቸውና መሰሪ ዓላማቸው በቂ እውቅና ስላልነበረው በሩን ከፍቶ ሰተት ብለው አስማራና አዲስ አበባ ባጭር ጊዜ ውስጥ እንዲገቡና የመንግስት ስልጣን እንዲይዙ ዝም ዝም ብሎ ተመለከታቸው። ደርግ ተገስሶ ህግሓኤ በኤርትራ/አስመራ፣ ህወሓት ደግሞ በኢህ አዴግ ስም በአዲስ አበባ የመንግስት ስልጣን በያዙ ማግስትም ትክክለኛ ማንነታቸውንና መሰሪ ዓላማቸውን በሚገባ ከጅምሩ የሚያውቁ የነበሩ በኢዴሃቅ ስር የተሰባሰቡትን ድርጅቶች በተለይ ደግሞ በወቅቱ በኢሃቅ ውስጥ በሁሉም መስኩ ከፍተኛ ሚና የነበረውና ሁለቱን ድርጅቶች ከስር መሰረታቸው የሚያውቃቸው ኢህ አፓ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ላንዴም ለመጨረሻውም ለማጥፋት የመንግስት ስልጣን በያዙ በማግስቱ ሰፊ የማጥፋት ዘመቻ በኢህ አፓ/ሰ ላይ ወዲያውኑ ጀመሩ።
በየነ ገበረ ተስፉ
ከፌስ ቡክ የተወሰደ